EthioLion

# የጥላሁን ገሰሰ ሞት የሀገርና የህዝብ ሀዘን ነው።

አገሬ ከስዊድን ሚያዝያ 2009

የዓለም ህዝብ ያንባ ፤ ሙሾ ይውረድ ወጥቶ

ጥላሁን ገሰሰ ፤ ደክሞት ሁሉን ትቶ

ላገር ለወገኑ ፤ ለአይነ ስጋ በቅቶ

ሁሌ እንደሚመኘው ፤ ገስግሶ አገር ገብቶ

ንጉሱ አሸለበ ፤ ለአገሩ አፈር በቅቶ

ገንቢ አስተሳሰቡ፤ ትምህርት ሰጭ ቃሉ

ሰው ሰው የሚያሰኘው ፤ ምግባር ማስተዋሉ

ሰርክ አስተማሪያችን ፤ ኪነጥበብ ውሉ

ሞት ነጥቆ ሲወሰደው ፤ ግሩም እስትንፋሱን

ትህትና ለዛ ፤ ግርማ ሞገስ ሀብቱን

የአገር መከራ ነው ፤ የወገን ሀዘን

ሀብት ንብረታችን ፤ ውዱ ጥላሁን

ገናና ስመጥር ፤ በአገር በወገን

EthioLion.Com

Ethiopia will prevail !

EthioLion

ሮስት ሆኗል ቃሉ ፧ በየልባችን

ናፍቆት ነው ሰቀቀን ፧ መለየት እሱን

የሀገሩ አለኝታ ፧ የጥቃቷ ጋሻ ፧ የችግሯ ደራሽ

ህዝበ ድምፅ አድራሽ ፧ የተራበ ዳባሽ

ዝንተ አለም ይሆናል ፧ ስራው ተወራራሽ

ብዙ ነው ውለታው ፧ ያላገኘው ምላሽ

ሀዘኑ ድርብ ነው ፧ በኢትዮጵያ ምድር

ዘፍኖና አንጎራጉሮ ፧ ያስደነቀው ሀገር

ንጉስ ነገረፈጅ ፧ ሲገባ መቃብርን

ነጋሪት ይጎሰም ፧ እንቢልታም ይመታ

ውስጣችን ተነክቷል ፧ ጥላሁን ሲረታ

EthioLion.Com

Ethiopia will prevail !